ሆቴሎች፣ሬስቶራንቶች እና የምግብ አገልግሎት የሚያቀርቡ ሌሎች ተቋሞች ለሠራተኞቻቸው የሚያቀርቡትን የምግብና የመጠጥ አገልግሎት ወጪ ሚኒስትሩ በመመሪያ ተቀናሽ እንዲደረግ በሚፈቅደው ልክ በአዋጁ አንቀጽ 22(1)(ሀ) መሰረት ተቀናሽ ይደረጋል፡፡

32.. **የንግድ ስራ ማስታወቂያ ወጪ**

በአገር ውስጥ ወይም በውጭ አገር የሚደረግ የንግድ ስራ ማስታወቂያ ወጪ ተቀናሽ የሚደረገው ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ በሚወስነው ገደብ ልክ ነው፡፡

33. **በራሱ ወጪ የተከራየውን ንብረት የሚያድስ/ የሚጠግን/የሚያሻሽል ተከራይ**

ከአከራዩ ጋር በገባው ውል መሰረት የተከራየውን የንግድ ስራ ሀብት በራሱ ወጪ የሚያድስ/ የሚጠግን/ የሚያሻሽል ተከራይ ለእድሳቱ/ጥገናው/ለማሻሻልያደረገው ወጪ ከንግድ ስራ ገቢው ላይ ተቀናሽ ይደረግለታል፡፡

34. **ለበጎ አድራጎት ዓላማ የሚደረግ ስጦታ**

1. በአዋጁ አንቀጽ 24(1) ለበጎ አድራጎት አላማ ለሚደረጉ ስጦታዎች የተፈቀደው የወጪ ተቀናሽ ግብር ከፋዩ ራሱ ለሚያካሂደው የበጎ አድራጎት ተግባር ለሚያውለው ወጪ ጭምር ተፈጻሚ ይሆናል፡፡
2. ለአዋጁ አንቀጽ 24(1)ለ አፈጻጸም በመንግስት የተደረገ ጥሪ ማለት በፌዴራል ወይም በክልል መንግስት የሚደረግ ጥሪ ሲሆን በአዲስአበባ እና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የሚደረግ ጥሪን ይጨምራል፡፡

35. **በዱቤ ሽያጭ ውል መሰረት በተያዘ የንግድ ስራ ሃብት ላይ የሚፈቀድ ተቀናሽ**

በዱቤ ሽያጭ ውል መሰረት ለተያዘ የንግድ ሥራ ሃብት የሚፈጸም የዱቤ ክፍያ ከጠቅላላ የንግድ ስራ ገቢ ላይ ተቀናሽ ይደረጋል ፡፡ሆኖም በዚህ አንቀጽ መሰረት ተቀናሽ የተፈቀደለት ሰው በንብረቱ ላይ የእርጅና ቅናሽ አይታሰብለትም፡፡

## ምዕራፍ ሁለት
## የእርጅና ቅናሽ

36. **ዋጋቸው የሚቀንስ ሀብቶች እና ግዙፋዊ ሀልዎት የሌላቸው ንግድ ሥራ ሀብቶች የእርጅና ቅናሽ**

ለ) በፊደል ተራ (ሀ) ከተመለከተው ውጪ ለሆነ ከ10 ዓመት በላይ ለሚያገለግል ግዙፋዊ ሀልዎት የሌለው የንግድ ሥራ ሀብት 10 በመቶ፣ ወይም

ሐ) ለሌላ ማንኛውም ግዙፋዊ ሀልዎት የሌለው የንግድ ሥራ ሀብት 100 በመቶን ግዙፋዊ ሀልዎት ለሌለው ሀብት የአግልገሎት ዘመን በማካፈል የሚገኘው መጣኔ፣

ይሆናል፡፡

3. ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም “ከአንድ ዓመት በላይ ጥቅም የሚሰጥ ወጪ” ማለት ግብር ከፋዩ የንግድ ሥራ ከመጀመሩ በፊት የሚያወጣው በአዋጁ አንቀጽ 25(7)(ሀ) ለ“ግዙፋዊ ሀልዎት የሌላቸው የንግድ ሥራ ሀብቶች” በተሰጠው ትርጉም ተራ ቁጥር (4) የተመለከተው ወጪ ነው፡፡

## 40. <u>በከፊል ለንግድ ስራ በዋለ ህንጻ ላይ የሚታሰብ የእርጅና ቅናሽ</u>

አንድ ህንጻ በንግድ ስራ ሃብትነት በከፊል በሚያገለግልበት ጊዜ የእርጅና ቅናሽ የሚታሰበው ለንግድ ስራ አገልግሎት በዋለው መጠን ብቻ ይሆናል፡፡

## 41. <u>ጥገናዎችና ማሻሻያዎች</u>

1. የንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ግብር ከፋይ በአንድ የግብር ዓመት ዋጋው በሚቀንስ ሀብት ላይ ላደረገው የጥገና ወይም ማሻሻያ ወጪ በግብር ዓመቱ የወጪ ተቀናሽ ይፈቀድለታል፡፡

2. በንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚፈቀደው የወጪ ተቀናሽ ሀብቱ በግብር ዓመቱ መጨረሻ ካለው የተጣራ የመዝገብ ዋጋ 20 በመቶ ሊበልጥ አይችልም፡፡

3. በንዑስ አንቀጽ (2) ከተጠቀሰው በላይ ያለ ማንኛውም የገንዘብ መጠን በሀብቱ የተጣራ የመዝገብ ዋጋ ላይ ይታከላል፡፡

## <u>ምዕራፍ ሦስት</u>
## <u>ኪሣራን ስለማሸጋገር</u>

## 42.. <u>ኪሣራን ስለማሸጋገር</u>

1. በአዋጁ መሠረት ከአንድ የግብር ዓመት በላይ የደረሰ ኪሣራ የተሸጋገረለት ግብር ከፋይ መጀመሪያ የገጠመው ኪሣራ በቅድሚያ ይቀነስለታል፡፡

እና ከዚሁ ገቢ ላይ ቀንሶ የሚያስቀረውን ማንኛውንም ግብር የሚያሳይ ሰነድመያዝ አለበት፡፡

## 58. በደረጃ "ሐ" ግብር ከፋዮች የሚከፈል ግብር

ለአዋጁ አንቀጽ 49 አፈጻጸም የደረጃ ሐ ግብር ከፋዮች በግምት ላይ የተመሰረተ መደበኛ የቁርጥ ግብር እና አመላካች ባላቸው የንግድ ስራ ዘርፎች የቁርጥ ግብር ዘዴዎች ግብር ይከፍላሉ፡፡

## 59. ግብር ተቀናሽ የማይደረግባቸው የአገልግሎት አይነቶች

ለአዋጁ አንቀጽ 92 አፈጻጸም ሚኒስትሩ ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብር ቀንሶ የመያዝ ስርዓት ተፈጻሚ የማይደረግባቸውን የአገልግሎት አይነቶች በመመሪያ ይወስናል፡፡

## 60. በሀገር ውስጥ ከሚፈጸሙ ክፍያዎች ላይ ግብር ቀንሶ ስለማስቀረት

1. በአዋጁ አንቀጽ 92 መሠረት ግብር ቀንሶ ገቢ የማድረግ ኃላፊነት የተጣለበት ሰው በዚሁ አንቀጽ መሠረት ግብር ተቀንሶ ክፍያ ለሚፈጸምለት ሰው ተከታታይ ቁጥር ያለው ሕጋዊ ደረሰኝ መስጠት አለበት፡፡
2. ግብር ቀንሶ ገቢ የማድረግ ኃላፊነት የተጣለበት ሰው የመንግሥት ተቋም ከሆነ በንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ደረሰኝ በሚኒስቴሩ መረጋገጥ አለበት፡፡
3. ከመንግሥት ተቋም በስተቀር በንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ ላለበት ግብር ቀንሶ ገቢ የማድረግ ኃላፊነት የተጣለበት ሰው የፌዴራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ 19 ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## 61.. ግብርን ቀንሶ የመያዝ ግዴታ ላለበት ሰው የንግድ ፍቃድ የማቅረብ ግዴታ

የአዋጁ አንቀጽ 92(4) ድንጋጌ ከግብር ከፋይ መለያ ቁጥር በተጨማሪ የንግድ ፈቃድ በማያቀርብ ሰው ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## 62. ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብር ቀንሶ መያዝ ስላላበት ሰው ኃላፊነት

1. ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብር ቀንሶ ለባለስልጣኑ የማስተላለፍ ግዴታ የተጣለበት ሰው ግዴታውን ያልተወጣ ቢሆንም ግብር ከፋዩ ግብሩን የከፈለ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ካቀረበ የአዋጁ አንቀጽ 97(3) ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ በታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ 106(1) የተጣለውን ቅጣት አያስቀርም፡፡

